ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)
Website: www.moreshwegenie.org E-mail: infoandpr@moreshwegenie.org

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *ረቡዕ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፩ዓ.ም.* *ቅጽ ፯ቁጥር ፲፫*

## በውጭ ሃገራት ለምንኖር ዐማራዎች የተደገሰልን
## በማር የተቀባ አደገኛ መርዝ

የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ትሕነግ)/ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ከአራት አስርተ ዓመታት በፊት የመገንጠል ትግሉን ሲጀምር የካቲት 1968 ዓ/ም በጻፈው የትግል ማኒፌስቶ ላይ የትግራይ ሕዝብ ጠላቶች ብሎ ከሰየማቸው አራቱ (4) ጠላቶች ቁጥር አንድ ብሎ በቀደምትነት ያስቀመጠው የዐማራን ሕዝብ ነበር፣ አሁንም ነው። ሌሎቹ ኢምፔሪያሊዝም፣ ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም (ጥገኛ ንኡስ ከበርቴ ሥርዓት) እና ፊውዳሊዝም ነበሩ።

ትሕነግ/ሕወሓት ከተመሠረተበት ከየካቲት 11 ቀን 1967 ዓ/ም ጀምሮ እስከ አለፈው ዓመት 2010 ዓ/ም ድረስ በዐማራው ሕዝብ ላይ ባካሄደው የዘር ማጽዳት ( ethnic cleansing) እና የዘር ጭፍጨፋ (genocide) ግምቱ ወደ 5.5 ሚሊዮን የሚገመት የዐማራ ወገኖቻችን አልቀዋል። ባለፈው ዓመት ትሕነግ/ሕወሓት ከሥልጣን እንዲለቅ ተደርጎ በሰራው ከፍተኛ ወንጀል ላይጠየቅ፤ የዘረፈውን የሃገር ሃብትና ንብረት ይዞ ወደ ትግራይ እንዲሸሽ ከተደረገ ጀምሮ በዐማራው ሕዝባችን ላይ በግልጽ የራሱን ሠራዊት በድብቅ በቅጥረኛ ኃይሎቹ የሚያከሂደው ጭፍጨፋ፣ ማፈናቀልና ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጦርነት እንደቀጠለ ነው።

የትሕነግ/ሕወሓት አፓርታይድ አገዛዝ አክተሞ፤ ለተረኞቹ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) የሥልጣን መንበሩ ተላልፏል። ይኸ የበግ ለምድ የለበሰው አታላይ ተኩላ የለውጥ ኃይል ነኝ የሚለው በዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ እየተመራ በሃገር ቤት እና በውጭ ሃገራት ያሉትን ኢትዮጵያውያን በማታለል በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ስም እየማለና እየተገዘተ እንዲሁም ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት እየሰበከና እየዘመረ ቀስ በቀስ የለበሰው የበግ ለምድ ሲገፈፍ ኦሕዴድ-ኦነግ (ኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር) ሆኖ በገሃድ ተከሰተ። ይህ የለየለት ፀረ-ዐማራው ኦሕዴድ-ኦነግ በረቀቀ ሴራ ዐማራውን መግደል፣ ማፈናቀል እና ማሰር በሰፊው ተያያዘው። ይኸም፣ የዐማራን ሕዝብ አንድነት ለማዳከምና ለማሽመድመድ ከተቻለ ደግሞ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ታቅዶ የሚሰራ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው፤ ከጥቂት ወራት በፊት የኦነግ ተዋጊ ኃይል በስውር በኦሕዴድ ሠራዊት መኮንኖች እየተመራ ሙሉ ትጥቅ፣ መገናኛ መሳርያ፣ ሕክምና ቆሳቁስ እና ምግብ ይዞ ከምዕራብ ወለጋ ተነስቶ እስከ አጣዬና ከሚሴ ድረስ በመዝለቅ ያልታሰበ ጦርነት በመክፈት ዐማራ ወገኖቻችንን ጨፍጭፎ፤ ቤት ንብረቶቻቸውን አቃጥሎ፣ ከቀያቸው አፈናቅሎ ማንም ሃይ ሳይለው በመጣበት መንገድ መመለሱ የሚታወቅ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ፤ ከፍተኛ ሴራ ተዶልቶ በተቀነባበረ መንገድ አርብ ሰኔ 14 ቀን 2011 ዓ/ም ከእኩለ ቀን ጀምሮ 5 የባሕርዳር ከተማ መውጫ ኬላዎች በልዩ መከላከያ ኃይል ተዘገተው፤ ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ/ም አራት(4) ከፍተኛ የዐማራ ክልል ባለሥልጣኖች በአሰቃቂ ሁኔታ በባሕር ዳር ከተማ ተገደሉ። በዚህ ሳቢያ፣ በዓለም ላይ ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ የዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ መንግሥት "መፈንቅለ-መንግሥት" ተካሄደ በማለት በዐማራ ክልል እና በመላ ሃገሪቱ መጠነ ሠፊ እስር ማካሄዱን ተያያዘው። ለዚህም በከፍተኛ ደራጃ ሰለባ የሆኑት በመላ ሃገሪቱ የሚገኙት የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) አመራር፣ አባላትና ደጋፊዎች፣ ታጋይ የዐማራ ተወላጆች፣ እንዲሁም ዐማራ ምሑራን፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ጋዜጠኞች፤ ሃበታሞች፣ ወጣቶች ወዘተ... ናቸው። አሁንም በዐማራው ላይ የሚካሄደው ወከባና እስር እንደቀጠለ ነው።

ሆን ተብሎ በዐማራው ላይ ይህ ዓይነት መጠነ ሰፊ እስርና ማሳደድ በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ እየተካሄደ፤ የለውጥ ኃይል በሎ እራሱን የሚጠራውና ለዐማራው ቁሜአለሁ የሚለው ብአዴን-አዴፓ ጆሮ ዳባ ብሎ ትላንት ለትሕነግ/ሕወሓት በአሽከርነት እንደቆመና እንዳገለገለ ሁሉ፤ ዛሬም የተጠናወተው የሎሌነት በሽታ አለቀው ብሎት ሽንጡን ገትሮ ለኦሕዴደ-ኦነግ አሽከርነት አድሯል።

በአሁኑ ሰዓት አሳሳቢ የሆነውን የሃገራችችን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀወስ፣ ከፍተኛ የሕዝብ መፈናቀልና ግጭት እሳቤ ውስጥ አስገብተን የዐማራው ሕዝብ የገባበትን ውጥንቅጦች በጽሞና ተመልክተን አንድና አንድ ወደ ሆነ ድምዳሜ ያደርሰናል።

# በውጭ ሃገራት ለምንኖር ዐማራዎች የተደገሰልን

## በማር የተቀባ አደገኛ መርዝ

በመጡኑ ለመጥቀስ ያህል፥

1ኛ/ በዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ የሚመራው ኦሕዴድ-ኦነግ በዐማራው ላይ የሚያከሂደው ጭፍጨፋና እስር፡

2ኛ/ ትሕነግ/ሕወሓት በዐማራው  ላይ የሚያካሂደው ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጦርነት እና ማፈናቀል፤

3ኛ/ ቀንደኛ  አነጋዊያን ትግራይ ድረስ ሂደው ከትሕነግ/ሕወሓት ጋር ሆነው በዐማራ ላይ የሚያሴሩት፤

4ኛ/ ሕስቅኤል ጊቢሳ በአንድ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ባደረገው ንግግር ወሎ "የኦሮሞ" ነው ብሎ በድፍረት መናገሩ፤

5ኛ/ ዐማራው ለኅልውናውና ለማንነቱ የሚያደርገው ትግል፤ የለየለት ፀረ-ዐማራው ሌንጮ ለታ (ዮሐንስ ለታ) "የዐማራው ብሔርተኝነት የበለይነት ፍለጋ ነው" ብሎ አሁን በቅርቡ ማስተጋባቱ፤

ከላይ በተጠቀሱት ሁኒታዎች አንጻር ፤ ኦሕዴድ-ኦነግ በድብቅ ከትሕነግ/ሕወሓት ጋር የገባበት ወይም ያደረገው ስምምነት እንዳለ ይጠቁመናል። በዚሁ መሠረት፤ የስምምነቱን አበይት ነጥቦች መገመት ይቻላል። እነርሱም፥

1ኛ/ የዐማራን ሕዝብ የመከላከል ኃይልና አቅም ማዳከምና ከጥቅም ውጭ ማድረግ፤

2ኛ/ የዐማራን የኅልውናና የማንነት ትግል ማጥፋት፤

3ኛ/ በጎንደር፣ በወሎ፤ በጎጃም እና በሸዋ የሚገኙትን የዐማራ መሬቶች በቀላል ወረራ መንጠቅ፤

4ኛ/ እንደ ዜጋ በመላ ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ የሚኖረውን ዐማራና ሌላውንም ኢትዮጵያዊ በማፈናቀል ከዘር የጸዱ  ክልሎች ለመፍጠር የሚደረገው ወከባና የሚፈፀመው ግፍ፤

4ኛ/ የዐማራን ሕዝብ በአንድ ጠባብ ክልል ከልሎ ማሰቀመጥ፤

5ኛ/ የኢሕአዴግ የሰራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አርብ ነሐሴ 3 ቀን 2011 ዓ/ም ባወጣው መግለጫ የግንቦት 2012 ዓ/ም ሃገራዊ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ቢያወጣም፤ ከአሁኑ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተን የሃገራችንን የእለት ከእለት ክስተቶች ስንገመግም፤ በእኛ እይታ የሚመጣው ግንቦት ወር 2012 ሃገራዊ ምርጫ ሰለማይካሄደና የኢሕአዴግ ሥልጣን ዘመኑ ስለሚያልቅ፤ በዚህ ትርምስ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አበረታችነትና ደጋፊነት የትግራይ ክልል በትሕነግ/ሕወሓት መሪነት በመጀመሪያ ተገንጥሎ ሲሄድ፤ ኦሮሚያ ክልል በበኩሉ የትግራይ መገንጠል እውን ሲሆን በኦሕዴድ-ኦነግ የበላይ አስተባባሪነት ተገንጥሎ ይሄዳል። ከዚያ በኋላ፣ ታላቁ የእርስ በእርስ ጦርነት በአራቱ የሃገሪቱ አቅጣጫ ይቀጣጠላል። የውጭ ጣልቃ ገብነትም እንደሚኖር ይገመታል።

በዐማራው ላይ ይህ ሁሉ ድግስ እየተደገሰለት፤ የዐማራውን ፋኖ ሕዝባዊ ትግል የእኔ ነው እያለ ዐማራውን ያስጨፈጨፈውና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያወናብድ የነበረው የትላንቱ የለየለት ፀረ-ዐማራው ግንቦት 7 ዛሬ ደግሞ የእርሱ ውላጅ የሆነው ዜግነት በሌለበት ሃገር እራሱን የኢትዮጵያ ዜጎች ማህበራዊ ፓርቲ (ኢዜማ) በሎ የሚጠራው ድርጅት አመራሮች የዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ ጽ/ቤት አጋፋሪዎችና ዘበኞች እንዲሁም የቤት ልጆች ሁነዋል። ኢዜማን ከበስተ ጀርባ የሚዘወረውና የሚደገፍው በሃገሪቱ መሪ ዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ ነው።

ኢዜማ በምርጫ ተወዳድሬ በከፍተኛ ድምጽ አሸንፍበታለሁ ብሎ ተስፋ ያደረገው በደቡብ እና በዐማራ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ነበር። ሆናም ግን፤ በመላ ሃገራችን እንደሰደድ እሳት የተቀጣጠለው የብሔርተኝነት ትግል በደቡብ ክልል በከፈተኛ ደረጃ ስለጦዘ የዜግነቱ ፓርቲ ኢዜማ ተቀባይነት እንደጉም ሰለበነነ፤ ኢዜማ ቦታ የለውም። ኦሕዴድ-ኦነግ አዲስ አበባ ከተማ የእኛ ነው ብሎ የባለቤትነት ጥያቄ ሲያነሳ፤ የዜግነቱን ፖለቲካ የሚያራምደው ኢዜማ ሸንጡን ገትሮ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች መብት መከራከር ሲገባው፤ የዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ አጋፋሪና ዘበኛ ስለሆነ ለአዲስ አባባ ሕዝብ መብት የሚታገለውን የባልደራስ ምክር ቤት መሪን፤ ጋዜጠኛና ሰብዓዊ መብት ተሟጋች እስክንድር ነጋን፤ የኢዜማ መሪ ዶ/ር በርሃኑ ነጋ በይፋ አውግዞ ታማኝነቱን ለኦሕዴድ-ኦነግ አረጋግጦ፤ እጋፋሪነቱን አስጠብቋል። በዚህ የተነሳ፤ የአዲስ አበባ ሕዝብ ኢዜማን ዓይንህን ለአፈር አለው። ሁለተኛ ሽንፈት።

በዚህ አኳኋን፤ ኢዜማ የመጨረሻ ተስፋውን የጣለው በዐማራ ክልል ነው። በዚሁ መሠረት፤ ዐማራ ክልልን ከብአዴን-አዴፓ ጋር በጋራ ለመጋራት ለዐማራ ኅልውናና ማንነት የሚታገለውን የዐማራ ብሔርተኝነት ሥር የተደራጁትን ድርጅቶች መሪዎችንና አባላት እንዲሁም የዐማራ ታጋዮችን ማስገደል፣ ማሳሰርና ማሳደድ የግድ ስለሚል፤ ከሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ የሆነው ይኸው ነው።

## በውጭ ሃገራት ለምንኖር ዐማራዎች የተደገሰልን

## በማር የተቀባ አደገኛ መርዝ

በዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ ከፍተኛ ድጋፍ ኢዜማ ከሰኔ 15 ቀን በኋላ በዐማራ ክልል እንደልቤ መጋለብ እችላላሁ ብሎ ስለአሰበ፤ ትኩረቱን በወጭ ሃገራት በሚኖረው  የዐማራ ተወላጆች አድርጎ፤ ዐማራው የሚጎዳው ስለአልተደራጀ ስለሆነ፤ በውጭ ሃገራት ያለውን የዐማራ ተወላጆች በአንድ ዐማራ ድርጅት ለማደራጀት በማቀድ ኢዜማ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ከፍተኛ ልዑክ ወደ አሜሪካ ልኳል።

ዋናው ዓላማ፣ በውጭ ሃገራት ለሚኖረው ዐማራ ተወላጆች የተቆረቆሩ መስለው በአንድ የዐማራ ድርጅት አዋቅረው በዘዴ የኢዜማ ቅጥያ ለማድረግና በእጅ አዙር በዶ/ር ኮሎኔል አብይ አህመድ ቁጥጥር ሥር ለማስገባት ነው። ስለዚህ በስሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ በአውስትራሊያና ኒውዜላድ እስራኤል እና መካከለኛው ምስራቅ የምትኖሩ የዐማራ ተወላጆች ይህን መሰሪ ተንኮል ተገንዝባችሁ በዚህ ማር በተቀባ አደገኛ መርዝ ወጥመድ ውስጥ እንዳትገቡ በጥብቅ እናሳስባለን።

ይኸን በማር የተቀባ የመርዝ ተንኮል ያልገባቸሁና በቅንነት በማየት ዐማራው እንዲደራጅ ብላችሁ ዐማራው በውጭ ሃገራት ተደራጅቶ አንድ ዓላም-አቀፍ ድርጅት መመሥረት አለበት ብላችሁ በየቦታው ስልክ እየደወላችሁ በቴሌኮንፈረስ  ስብሰባዎች የምትጠሩ ከዚህ ተግባር እንደትቆጠቡ በዐማራ ሕዝብ ስም በጥብቅ እንጠይቃለን።

በውጭ ሃገራት የተበተንከው ዐማራ ወገናችን ሆይ! በአባቶቻችንና በእናቶቻችን የዛሬ 490 ዓመት የመጣባቸው ከበባና ጭፍጨፋ በአንድ አቅጣጫ ነበር። የዛሬው ከበባ ለየት የሚያደርገው በሁለት (2) አቅጣጫዎች ከሰሜንና ከደቡብ መሆኑ ነው። ይህን የከበባ ጦርነት የሚያካሂዱት የዐማራው ጣምራ ጠላቶች የሆኑት ትሕነግ/ሕወሓት እና ኦሕዴድ-ኦነግ ናቸው። ይኸን ከወዲሁ ተረድተህ በያለህበት እውነተኛ የዐማራ ወገኖችህን እያፈላለክ ተደራጅ፣ በያለህበት የፕሮፓጋንዳ ዘመቻህን አጧጥፍ፤ ቆራጥ የዐማራ ወገኖችህ ያቋቋሙትን የዐማራ ድምጽ ራዲዮ (ዐድራ) የዐማራ ሚዲያ ማዕከል (ዐሚማ) ቲቪ እና አሥራት የዐማራ ቴሌቪዥን በተቻለህ መጠን እርዳ፤ ሃገር ቤት ያለውን ትግል ደግፍ።

በዐማራው ሕዝባችን የሚያንዣብበውን ከፍተኛ አደጋ ተገንዝበን በደንብ የምንተዋወቅና የምንተማመን በውጭ ሃገራት የምንገኝ የዐማራ ድርጅቶች፤ ማህበራት፣ ታጋዮች፤ ምሑራን፣ ወጣቶች ወዘተ... በአስቸኳይ መሰባሰብ ግድ የሚለን ወቅት ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው። ተመስርተው ወገናችንን እያገለገሉ ያሉትን የዐማራ የሲቪክ፣ የሚዲያና፣ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያላቸውን ታሪክ የሥራ ወጤት እና ለወገናችን ለመቆም ያሳዩትን ጽናት በሚቻለን ሁሉ በመመርመር፤ ቢያንስ እንርዳቸው፤ በመርዳት ጠንካራ የአማራ ተቋማት እንዲሆኑ እንድናደርጋቸው ለሁሉም ዐማራና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን።

አራቱ (4) በግፍ የተገደሉት የዐማራ ክልል መሪዎች ድምጽ፤ ዐማራው ተነስ! ከላይና ከታች የመጣብህን ከበባ ተቋቁመህ ኅልውናህንና ማንነትህን አስጠብቅ እያለ ከመቃብር ላይ ይጮሃል።

በቆራጥ ጀግንነት ለዐማራ ሕዝባችን ኅልውና፣ ማንነትና ልዕልና ሲል የተሰዋውና በዐማራ ሕዝብ ልቦና ዝንተዓለም የሚኖረውን የጄኔራል አሳምነው ጽጌ ቃል አክብረን እንጠብቅ።

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ<br>
ሁሉም ዐማራ ለአንድ ዐማራ!<br>
የዐማራው ሕዝብ ኅልውናና ማንነት በጀግና ልጆቹ ይከበራል!<br>
ጀግናው አሳምነው ጽጌ የትግላችን ቀንዲል ነው!<br>
ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃልኪዳን ነው!